# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

ሰመጉ

## አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ

ሰኔ 24 ቀን 2008 ዓ.ም

## በአዲስ አበባ ከተማና አካባቢው ዜጐችን ከቤት ንብረት የማፈናቀል ድርጊት ይቁም!

በአዲስ አበባ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች ዳርቻና አካባቢ በተለያየ ጊዜና በተለያየ መንገድ ቦታ ይዘው ቤት ሠርተውና ቤተሰብ መሥርተው ኑሮአቸውን የሚገፉ በርካታ ዜጎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ከነዚህ ዜጎች አብዛኛዎቹ ካርታ ባይኖራቸውም፣ ለረዥም ዓመታት ቦታውን በይዞታነት ግብር ሲከፍሉበት የቆዩ፣ መብራትና ውኃ የመሳሰሉ አገልግሎቶች በመንግሥታዊ ተቋማት ሲያገኙ የቆዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ዜጎች ከጅምሩ ከከተማዋ ማስተር ፕላን ጋር በሚጋጭ ሁኔታ ግንባታ እንዳያደርጉ ሌላ ሕጋዊ አማራጭ ሊያመቻችላቸው ሲገባ፣ ከሆነም በኋላ ከማስተር ፕላኑ ጋር በተጣጣመ መልኩ ሕጋዊ ሥርዓት ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፣ ወይም ተለዋጭ የመኖሪያ ቦታዎች ማዘጋጀት ሲገባ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከከተማዋ ማስተር ፕላን ጋር አይጣጣምም በሚል ምክንያት በርካታ ቤቶችን "ሕገ-ወጥ" ናቸው በማለት በአፍራሽ ግብረ ኃይል አማካኝነት በማፍረስ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ እርምጃው እየተወሰደ ያለው ክረምት እየገባ ባለበት ወቅት በመሆኑ በፈረሱት፣ እየፈረሱ ባሉትና ለማፍረስ ዕቅድ በተያዘባቸው በጣም በርካታ ቤቶች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ፣ ሕጻናትን፣ ሴቶችና አረጋውያንን ጨምሮ በዐሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጐች ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው ይገኛሉ፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 32 (1) "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ በሐገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሐገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት ነፃነት አለው" ሲል ይደነግጋል፡፡ የሕገ -መንግሥቱ አንቀጽ 40 (7) እና (8) ደግሞ ማንም ሰው በመሬት ላይ የሚገነባው ቋሚ ንብረት ባለቤት እንደሆነና መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለመውሰድ የሚችለው በቅድሚያ የካሣ ክፍያ ፈጽሞ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ በተቀበለችው የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 11(1) እያንዳንዱ ሰው በቂ ምግብ ልብስና መጠለያ ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ ኑሮ የማግኘት መብት አለው በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ መንግሥት ደግሞ የዚህ መብት ተነፃፃሪ ግዴታ እንዳለበት በዚህ ቃል-ኪዳን ላይ ተገልጾአል፡፡

የአፍሪካ የግለሰቦችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 21፣ ማንኛውም ሰው ያፈራውን ሀብቱንና የተፈጥሮ ሀብትን በነጻነት የመጠቀም ሙሉ መብት እንዳለውና ያላግባብ የተወሰደ ንብረት ካለውም እንደሚመለስለት እንዲሁም በቂና ተመጣጣኝ ካሣ የማግኘት መብት እንዳለው



የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ Human Rights Council

ደንግጓል። ኢትዮጵያም የዚህ ቻርተር ፈራሚ አገር በመሆኗ መንግሥት ይህንን መብት እንዲያከብርና እንዲያስከብር ግዴታ ተጥሎበታል።

ይሁን እንጂ ከላይ እንደተመለከተው፣ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከከተማዋ ማስተር ፕላን ጋር አይጣጣምም በሚል ምክንያት በርካታ ቤቶችን "ሕገ-ወጥ" ናቸው በማለት በአፍራሽ ግብረ ኃይል አማካኝነት በማፍረስ ላይ እንደሚገኝ የመብት ጥሰት ደረሰብን የሚሉ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለሰመጉ በአካል ቀርበውና በተወካዮቻቸው አማካኝነት በማመልከት ላይ ይገኛሉ።

ከነዚህ መካከል በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ስሙ ወረገኑ በሚባል ቦታ ላይ ለበርካታ ዓመታት ቤት ሠርተው፣ ትዳር መሥርተው የሚኖሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ይገኙበታል። ከነዚህ ዜጎች በርካቶቹ ለሰመጉ እንዳስረዱት፣ መብራት እንዲገባላቸው ከቦሌ ክፍለ ከተማ የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎላቸዋል። የውኃ አገልግሎትንም በሚመለከት አራት የውኃ ቦኖዎች ገብቶላቸዋል። ነዋሪዎቹ በየአካባቢያቸው እድር መሥርተው በእድሩ ስም በአባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ለሚገኘው ግድብ ቦንድ ሲገዙና ለልማት ገንዘብ ሲያዋጡ ቆይተዋል። ከቦሌ ክፍለ ከተማ ከሚመጡ የመንግሥት ኃላፊዎችና ተወካዮችም ጋር በተለያየ ጊዜ በልማት፣ በምርጫና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ሲያደርጉና ሲሳተፉ ቆይተዋል። የአካባቢው ባለሥልጣናትም የቦታ ማረጋገጫን በሚመለከትም በቦሌ ክፍለ ከተማ ከወረዳ 12፣ ሰው ያልገባባቸው ጅምር ቤቶችና በ2008 ዓ.ም የተሠሩ ቤቶች እንደሚፈርሱ፣ የሊዝ ዐዋጁ በ2004 ከመውጣቱ በፊት የተሠሩ ቤቶች በአየር ካርታ እንደተነሡና በዚሁ መሠረት እንደሚስተናገዱ እንደተገለጸላቸው ነዋሪዎቹ ይገልጻሉ።

ነገር ግን ከግንቦት 13 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ጋዜጣዊ መግለጫ እስከወጣበት ሰኔ 24 2008 ዓ.ም ድረስ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከሊዝ ዐዋጁ በፊት የተሠሩትን ቤቶች ጨምሮ በ10,000 (በዐሥር ሺህዎች) የሚቆጠሩ ቤቶች ፈርሰው ቆርቆሮ፣ በርና መስኮታቸው እየተነቃቀለ በአፍራሽ ግብረ ኃይል መወሰዱን ተጎጂዎቹ ነዋሪዎች አመልክተዋል። ይህ የማፍረስ ሂደት ትዕግሥት የጎደለውና ኃይል የተቀላቀለበት በመሆኑ ለሰዎች መሞት፣ መቁሰል፣ መታሠርና መፈናቀል መንሥኤ መሆኑን የጉዳቱ ሰለባዎች ለሰመጉ ገልጸዋል። የሰመጉ ባለሙያዎችም በቦታው ድረስ በመሄድ የፈረሱ ቤቶችን ተመልክተው የደረሰውን ጉዳት ያረጋገጡ ሲሆን፣ ደረሱ የተባሉትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሰመጉ በዝርዝር በማጣራት ላይ ይገኛል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀጠና 01 መንደር 06፣ በተለምዶ አጠራር ቀርሳና ኮንቶማ፣ ቁጥራቸው 9617 የሚደርስ አባወራዎች በጠቅላላ 19264 ነዋሪዎች ከ10 እስከ 15 ዓመት ከኖሩበት ቦታ ‹‹ሕጋዊ አይደላችሁም፣ ቦታው ለቁራ አገልግሎት ስለሚፈለግ ልቀቁ›› መባላቸውንና ለተለያዩ የመንግሥት አካላት ቢያመለክቱም መፍትሔ አለማግኘታቸውን ገልጸው ለሰመጉ አመልክተዋል።

በተጨማሪም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ኢርቱ ተክለሐይማኖት ቀጠና 4፣ ከ250 በላይ አባ ወራዎች ለበርካታ ዓመታት በአካባቢው የኖሩ እና ከክፍለ ከተማውና ከወረዳው ጋር በመሆን በምርጫ፣ በልማት፣ በመንገድ ሥራ፣ መብራት በማስገባትና በጸጥታ ጉዳዮች በጋራ



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

ሲሠሩ የቆዩ ቢሆንም ያለምንም ማስጠንቀቂያ በግንቦት 29/2008 ዓ.ም ቤታቸው ከነሙሉ ንብረቱ በአፍራሽ ግብረሃይል መፍረሱን በመግለጽ ተጎጂዎች ለሰመጉ በጽሑፍ አመልክተዋል፡፡

በተመሳሳይም በዚሁ ኤርቱ ተክለሃይማኖት አካባቢ የሚኖሩ ሌሎች 169 የቤተሰብ ኃላፊዎች ‹‹ከ2000 ዓ.ም በፊት ከአካባቢው ገበሬዎች ውል በመግባት ጅምር መኖሪያ ቤትና ይዞታ ገዝተን ቤተሰብ መሥርተን እየኖርን እንዳለን የክፍለ ከተማው የወረዳ 1፣ ለቡ አካባቢ ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት፣ ቤታችንን በ24 ሰዓት ውስጥ አፍርሰን እንድንሄድ ማስጠንቀቂያ በየቤታችን ለጥፎ ንብረታችንን ለማውጣት እንኳ በቂ ጊዜ ሳይሰጠን መኖሪያ ቤቶቻችን በመፍረሳቸው በከፍተኛ ችግር ላይ እንገኛለን›› ሲሉ በጽሑፍ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡ ሰመጉም ችግሩን በቦታው ድረስ ባለሙያዎችን በመላክ የደረሰውን ውድመት ተመልክቷል፡፡ ጉዳዩንም በዝርዝር በማጣራት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የካ አባዶ እና ሐና ማርያም አካባቢ የሚገኙ በርካታ ቤቶች ከዚህ ቀደምም ፈርሰዋል፣ አሁንም በመፍረስ ላይ ናቸው፡፡

ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች፣ ቤታቸውን ሠርተው መብራትና ውኃን ለመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች ብዙ ገንዘብና ጉልበት አፍስሰዋል፡፡ የከተማው አስተዳደር ያወጣውን የሠነድ-አልባ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያን በመተማመን መፍትሔ እየተጠባበቁ በሚገኙበት ጊዜ በድንገትና በተለይም ዝናብና ብርድ በሚበረታበትና በበረታበት በክረምት ወቅት ቤቶቻቸው ያለምንም ካሣ ፈርሰውባቸዋል ወይም እየፈረሱባቸው ይገኛል፡፡ በዚህ ዓይነት ድርጊት ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ በጣም በርካታ አባወራዎች ከነቤተሰቦቻቸው መውደቂያ አጥተው ለቁር፣ ለልዩ ልዩ ችግርና አደጋ ተጋልጠዋል፡፡ ቤተሰብም እንዲበታተን፣ ብዙዎች ወደ ጐዳና ኑሮ እንዲወጡና ልጆቻቸውም ትምህርት እንዲያቋርጡ ምክንያት ሆኗል፡፡

እየተፈጸመ ያለው ድርጊት ሕገ-መንግሥቱንና ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የፈረመቻቸውን የተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች በተለይም የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንን በግልጽ የሚፃረር ነው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ - ሰመጉ ዜጎችን ከመኖሪያ ቤታቸው ማፈናቀልን በመቃወም በተለያዩ ጊዜያት መግለጫ ማውጣቱ የሚታወስ ነው፡፡ አሁን እየተፈጸመ ያለው ድርጊት ግን መንግሥት ለችግሩ፣ ለሕገመንግሥታዊ ግዴታዎቹና ለሰመጉም ጉትጎታ በቂ ትኩረት እንዳልሰጠ የሚያሳይ ነው፡፡

ዜጐች ለበርካታ ዓመታት ቤት ሠርተው፣ ትዳር መሥርተው ከሚኖሩበት ኑሮ፣ ከሕዝቡ ጋር በቂ ምክክር ሳይደረግና በተለይም በክረምት ወቅት ቤቶችን የማፍረሱ ሂደት፣ የዜጎችን መጠለያ የማግኘት መብት፣ ሰብዓዊ ክብርና ብሎም የመኖር ዋስትናቸውን ጭምር የሚጻረር ነው፡፡ ድርጊቱ በአካባቢው የሚገኙ ህጻናት ትምህርታቸው እንዲስተጓጎል የሚያደርግ እና የመማር መብታቸውን የሚጋፋ፣ ዜጎችን በክረምት ጎዳና ላይ ወድቀው ለጤና ችግሮች የሚዳርግና የጤና መብታቸውንም የሚጎዳ በመሆኑ ባስቸኳይ እንዲቆም ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

በተጨማሪም ድርጊቱ አላስፈላጊ ወደሆኑ ግጭቶች እና ተያያዥ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እያመራ ነው፡፡ በመሆኑ ፡



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

- መንግሥት በግጭቱ ለዜጎች ሕይወት መጥፋት፣ አካል መጉደል እና ንብረት መውድም ተጠያቂ የሆኑ አካላትን ለፍርድ እንዲያቀርብ፣
- ጉዳዩን የአዲስ አበባ መስተዳድር አሁንም በትዕግሥትና በሰከነ መልኩ ሕዝቡን በማወያየት እና ለዜጎች ተለዋጭ  የመኖሪያ ቦታ በማመቻት ሰላማዊ መፍትሔ እንዲሰጠው፣
- ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት የዜጎችን አስከፊ መፈናቀል እንዲያቆም፣
- ጉዳዩ በጥንቃቄ ተጠንቶ ካሣ ለሚገባቸው ሁሉ እንዲከፈል እንዲደረግ፣
- ቤታቸው ለፈረሰባቸውና በየቦታው ተበትነው ለሚገኙ ዜጎች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ሁሉ ሕጋዊ፣ ሰብዓዊና ቁሳዊ እገዛ፣ እርዳታና መፍትሔ እንዲሰጧቸው ሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ለወደፊቱም መንግሥት ችግርን በመከላከል ላይ ያተኮረ፣ የተጠና፣ በሚገባ የታቀደና የተቀናጀ የቤቶች ልማት የአሰራር ሥልት እንዲጠቀም የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ሰመጉ አበክሮ ያስስባል፡፡ ሰመጉ ጉዳዩን በጥልቀት በመመርመር ላይ መሆኑንና እንደተጠናቀቀም ልዩ መግለጫ የሚያወጣ መሆኑን በድጋሚ ያስታውቃል፡፡

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council